

# አስሩ ለምፃሞች

- ለምፅ እጅግ በጣም አስከፊ በሽታ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ ከሰው ወደሰው ይተላለፋል። ይህም ማለት ጤነኞች የነበሩ ሰዎች በሽታው ሊተላለፍባቸው ይችላል። በዚያን ዘመን አንድ ለምፃም ሊከተላቸው የሚጠበቅበት ሕጎች ነበሩ። ለምፁ ወደ ሌሎች ሰዎች እንዳይተላለፍ ለምፁ ያለበት ሰው ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ርቆ በሌላ ሰዎች በማይኖሩበት አካባቢ እንዲኖር ይገደድ ነበር። ቁስል ብጤ በአንድ ሰው ላይ ቢታይ ያ ሰው ወደካህን ይቀርብና ካህኑ ይመረምረዋል። ካህኑ ሰውዬው ለምፅ የለበትም ካለ ብቻ ከቤተ ሰቦቹ ጋር እንዲቀላቀል ይፈቀድለታል።

- አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን ካለመታዘዛቸው የተነሳ የለምፅ በሽታ ይይዛቸዋል። የሙሴ እህት ማሪያምና አሮን ወንድሟ እግዚአብሔር ልክ በሙሴ እንደሚናገር በእነርሱም ይናገራል በማለታቸው የለምፅ በሽታ እንደያዛት መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን።

- አንድ ንጉስ በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ለምፅ ያዘው። የዚህ ንጉስ ስሙ ኦዝያን ይባላል። እርሱም የአይሁድ ንጉስ ነበር። ይህ ንጉስ መንገስ በጀመረበት ጊዜ እጅግ መልካም ሰው ነበር። ኋላ ኋላ ግን ማመፅ ጀመረ። እናም በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ እጣን ለማጠን ወሰነ። ይህን ማድረግ የሚችሉት ካህናት ብቻ ነበሩ። እሱ ደግሞ ካህን አልነበረም፤ ንጉስ እንጂ። በዚህ ምክንያት በቀሪ የሕይወት ዘመኑ ለምፃም ሆኖ ለብቻው በአንድ ቤት ውስጥ ከሰው ተለይቶ መኖር ጀመረ።

- ዛሬ የምናየው የለምፃሞች ታሪክ የተፈፀመው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደኢየሩሳሌም እየተጓዘ በነበረበት ወቅት ነበር። ለምፃሞቹ ከኢየሱስ ጋር ተገናኙ፤ ሆኖም በርቀት ቆሙ። ለምፃም ሰዎች ወዳሉበት አካባቢ

አይቀርብም፤ ደግሞም፣ “ለምፃም ነኝ፣” እያለ ሌሎች ሰዎች እንዳይጠጉትና ለምፅ እንዳይተላለፍባቸው ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ነበረበት።

- እነኝህ በቁጥር አስር የሚሆኑ ለምፃችም ፣ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ማረን!” እያሉ ጮኹ። ሌሎችን ለምፃሞችን እንዳነፃቸው ያውቃሉ።

- ኢየሱስም እንዲሄዱና ራሳቸውን ለካህን እንዲያሳዩ አዘዛቸው። በመንገድ ላይ ሳሉም አሰደናቂ ነገር ሆነ። ቆዳቸው ንፁህ ሆነ። ለምፃቸውም ለቀቃቸው። መቼም የተሰማቸውን ደስታ ማሰብ እንችላለን።

- ዘጠኙ ሰዎች ጉዟቸውን ወደ ካህናት ቀጠሉ። አንደኛው ግን ወደኢየሱስ ተመለሰ። እግዚአብሔርን በታላቅ ድምፅ እያመሰገነ በኢየሱስ እግር ስር ተደፍቶ ሰገደለት፣ አመሰገነውም። ይህ ሰው ሳምራዊ ሲሆን የመጣውም ከሰማርያ አካባቢ ነበር። በዚያን ዘመን ሳምራውያን በአይሁዳውያን አይወደዱም ነበር።

- ኢየሱስም ሌሎቹ ዘጠኝ ሰዎች የት እንዳሉ ጠየቀ። አስር ለምፃሞች ተፈውሰው ነበር። ከእነርሱ ግን ለምስጋና የተመለሰው ይህ እንግዳ ወገን ብቻ እንደሆነ ኢየሱስ ተናገረ።

- ሰውዬውንም፣ “ተነሳና ሂድ፣ እምነትህ አድኖሃል፣” አለው።

*.የአስሩ ለምፃሞች መፈወስ ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17፡ 11 – 19 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com